# ★ ዴሞክራሲያ ★

*****************************************************

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

*****************************************************

ዴሞ ቅጽ 36፣ ልዩ ዕትም — ታህሣስ 2003


## ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሁልጊዜ ሲያለቅስ ይኖራል

ሀገርን ከውርደት፣ እራስን ከባርነት ለመጠበቅ፣ የውጭ ጠላት ድንበርን ሰብሮ ለመግባት በሞከረ ቁጥር በድንበር ያሉት ቀዬዎች ተወላጅ ዜጋ ብቻ ሳይሆን በመላው ሀገሪቱ ያለው የነፃነት አርበኛ በትክሻው የሚያንጠለጥላትን ስንቁን ብቻ ቋጥሮ፣ እግሩ እስኪነቃ ለሳምንታትና ለወራት ተጉዞ፣ አገር አቋርጦና ወንዝ ተሻግሮ የእናት አገሩን ድንበር ከወራሪ፣ ለመከላከል ይዘምታል። ለሀገሩ ዳር ድንበር መከበር ህይወቱን አሳልፎ የሰጠው ኢትዮጵያዊ ቁጥር በአዕላፍ የሚቆጠር ነው፤ ወደር የማይገኝለት መስዋዕትነት! ኢትዮጵያ እስከ ሁለንተናዋ አሁን ላለው ትውልድ ለጋራ ባለቤትነትና የጋራ ሃላፊነት የተላለፈችው በዚህ አባቶቻችንና እናቶቻችን በከፈሉት ዕፁብ ድንቅ በሚባል የጋራ መስዋዕትነት ነው።

ዓባይ ወንዝ ከሀገራችን ተራሮቿ ፈልቆ ለም አፈሯን ጠራርጎ፣ እየሰረሰረና እያጠበ በዓለም ረጅሙን የወንዞች ጉዞ ተጉዞ፣ ለሱዳኖችና ለግብፆች የህይወት ዋስትና ሰጥቷቸዋል። ኢትዮጵያ የዓባይ ወንዝ እናት በመሆኗና የስዊስ ባሕረ ሰላጤ ከተከፈተ በኋላም፤ እኒህ ህወሓትና የኤርትራ ሕዝባዊ አርነት ግንባር (ሻዕቢያ) የሚባሉ ከሃዲዎች የተቆጣጠሯቸው ድርጅቶች እስኪፈጠሩ ድረስ፤ አፍሪካንና መካከለኛው ምሥራቅን በመስንጠቅ ዓለም አቋራጭ የንግድ መተላለፊያ አድርጎ የሚገለገልበት የቀይ ባህር ባለቤት በመሆኗ፣ ለረጅም ዘመናት የውጭ ትኩረትን እንድትስብና ለጥቃት ዒላማ እንድትሆን ሲያደርጋት ኖሯል። ቱርኮችንም ሆነ ግብፆችን በማገዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ የባህር በሩን እንዳይቆጣጠር ሲጥሩ የኖሩት ምዕራባውያንም፣ እራሳቸው አፍሪካን ለመቀራመት ሲነሱ ያለማቋረጥ ሀገራችንን የጥቃት በትራቸው ማረፊያ ሲያደርጓት ኖረዋል። ይህን የንግድ መስመር እንደፈቀዳቸው ለመጠቀምም ኃያላኑ መንግሥታት ወገን ለይተው እርስ በርሳቸው በሚያደርጉት ሽሚያና ትርምስ ይህ አካባቢ የሌላው ጉልበተኛ ሀገር ተባባሪ እንዳይሆን ሲያሜሩባቸው ኖረዋል። በተለይ የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት በቀይ ባህር ዙሪያ ያሉት ሀገሮች ሰላም የሰፈነባቸው ሆነው የተጠናከረና እያንዳንዱ ሀገር የራሱ ብሄራዊ ስሜት ኑሮት የሀገሩንና የሕዝቡን ጥቅም በማስቀደም ሊከላከልና ሊያስከብር የሚሞክር መንግሥት እንዳይኖረው ከፍተኛ ደባ ሲፈጽሙ ኖረዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በመደጋገም ወራሪዎችን አይቀጡ ቅጣት እየቀጣና እያሳፈረ በመመለሱ ጀግንነቱን እንዲገነዘቡ የተደረጉት የሀገራችን ጠላቶች፣ ሃገሪቱን

ለማዳከምና ለማንበርከክ የተጠቀሙበት ዋነኛው ሤራቸው ሕዝቡን መከፋፈልና አንድነቱን ለማናጋት መሞከር ነበር። ዛሬ መለስ ዜናዊ የሚጠቀምበት ከሞላ ጎደል የጣሊያን ፋሽስቶች ሀገራችንን በወረሩበት ወቅት ነድፈውት የነበረውን በዘር የመከፋፈያ ዕቅድ ነው። ሕዝባችን ያለውን የተለያየ ቋንቋና ዕምነቶች እንደ ልዩነት በማጉላትና ለመከፋፈያነት በመጠቀም የሚቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። በጠላት ጥቃት ላይ እንዳያተኩርና በልማት ሥራዎች ላይ እንዳይሰማራ፣ እርስ-በርሱ እንዲጋጭና በውስጥና በውጭ ጦርነቶች ላይ እንዲወጠር ለማድረግ በርካታ ሤራዎች ሲያጠነጥኑ ኑረዋል። ዛሬም ይህንኑ ተንኮላቸውንና ሤራዎችን መተብተባቸውን እንደቀጠሉ ናቸው።

ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን የጠላት የደረጀ ጦር ብዛትና በመሣርያ ጥራት መብለጡ ሳያግዳቸው፣ በቆራጥነት ጠላትን ሲያርበደብዱት በወዳጆቻቸው ብቻ ሳይሆን በጠላቶቻቸውም የተፈሩና የተከበሩ ነበሩ። ኢትዮጵያችን "የሀገሬ ባንዲራ ስትረገጥ በዓይኔ አላይም" በማለት፣ በሰይፍ የጠላትን አንገት በመቅላት ሮማን በደም ያቀለመው ጀግናም ሀገር ናት። "መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል" እንደሚባለው ዘርዓይ ደረስን የመሰሉ ጀግኖች ከተፈጠሩባት የሃገራችን ማህፀን የተወለዱና በማንነቷ ላይ የተነሱ፣ ከማንነታቸው በላይ የወራሪ ጠላትን ባህልና ማንነት ተከናንበው፣ እራሳቸውን ረግመው፣ ጥቅም ሊሰጡን ይችላሉ ያሏቸውን ሁሉ መስለውና ለእነሱም በሎሌነት አድረው፣ በሕዝባቸው የሺዎች ዓመታት ታሪክ ተዘባብተው፣ በህልውናዋ ላይ ዶልተውና አሢረው፣ የሕዝብን መብትና ሉዓላዊነት ነፍገው፣ እንደ ደዌ ውስጧን እየሰረሰሩ፤ አንድነቷን በማዳከምና ሕዝቡንም በመከፋፈል ተግባር ላይ የተሰማሩ ከሃዲዎችንም ፈጥራለች።

ባልተቋረጠ የእጅ-አዙር ጦርነትና ትንኮሳ ሀገራችንን ለማጥቃት ጥረት ስታደርግ የነበረችው ግብጽም፣ አያሌ የቀድሞ ሙከራዎችዋ አልተሳኩላትም ነበር። እንዲያውም ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ማዕከል ሆነች፣ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ይዞታና ወሰኖችዋም በአፍሪካ አንድነት እውቅና ሲያገኙና ኤርትራም ከኢትዮጵያ ጋር ፌደራላዊ ትሥሥር ማድረጓ ሲረጋገጥ፣ ሀገር-በቀል የሆኑ ፀረ-አንድነት ኃይሎችን በማበረታት፣ በመደገፍና በማስታጠቅ የመከፋፈል ጥንስስዋን በኤርትራ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ፀረ-አንድነት ስሜትና የመገንጠል ፍላጎት ሥር እንዲሰድ የሚቻላትን ሁሉ አደረገች። ቀደም ብለው የቀይ ባህርን "የዓረብ ባህር" በማለት ስያሜውን ለመለወጥ ሲጥሩ የነበሩ ሌሎች የዓረብ ሃገሮችም ይህ በግብጽ አጋዥነት የተጀመረው ሃገራችንን የማጥቃት ጅምር እራሳቸው ካላቸው ከፊሉን ሕዝባችንን "የዓረቡ ክፍል ተቀጥላ የማድረግ" ፍላጎትና ህልም ጋር ተጣጥሞ ስላገኙት ፀረ-አንድነቱን ኃይል በማጠናከርና በመርዳት በሀገራችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገሩ አንድነት ቀናዒ በመሆኑ ከመሪዎቹ ጋር ሆኖ በጀግንነት ያደረገው ተጋድሎ ሀገሪቱን በነፃነት እንድትቀይ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ በየጊዜው ሀገሪቱን የገዟት እነዚሁ መሪዎች በመላ የሃገሪቱ ሕዝብ ላይ ጭቆናን በማስፈንና አስተዳደራዊ ግፍና በደሎችን በመፈፀም ሕዝብ ለአንድነቱ ያለውን ፍቅር በእኩልነትና በፍትኅ ጽኑ መደላድል ላይ እንዲቆም ለማድረግ የተደረጉ ሙከራዎችን በመፃረር ሕዝቡ በምሬትና ባልተቋረጠ ስቃይ ውስጥ እንዲኖር አድርገዋል።

ድርጅታችን ኢሕአፓም ህልው ከሆነበት ጊዜ አንስቶ ይህንን በደልና የፍትኅ መዛባት ለማስወገድ ታግሏል፤ ብርቱ መስዋዕትነትም ከፍሎበታል። የእኩልነት፣ የፍትኅ፣ የመብት፣ የዕድገትና መሻሻል … ጥያቄዎች በተለያዩ ወቅቶች በአግባቡ ተነስተዋል። ሁሉም ሕዝብ ተበዳይ ነውና፣ ኢሕአፓ በተባበረ ትግል የበደልና የግፍ አገዛዝን አስወግዶ በምትኩ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ሥርዓት ለመትከልና የዜጎች እኩልነት የተረጋገጠባት፣ ሀገራዊ አንድነቷ የተከበረ ኢትዮጵያን ለመመሥረት በጽናት ታግሏል፤ አታግሏልም። አሁንም ሳያለሰልስ ትግሉን እንደቀጠለ ነው።

ከጣሊያን ወረራ ጋር ከተያያዘ የቅርብ ታሪክ አኳያ የኤርትራ ጉዳይ አወዛጋቢ ጥያቄ ሆኖ መቆየቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ዘላቂ ሰላም፣ እድገት፤ ብልጽግና በኤርትራም ሆነ በቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ዋስትና ሊያገኝ እንዲችል መፍትሄዎቹ ሁሉ ከዴሞክራሲዊ መተክል የመነጨ፣ ሕዝባዊ ፍላጎትን ያረጋገጡ መሆን እንዳለባቸው ኢሕአፓ በየጊዜው አመላክቷል። ይህ የቆየ አቋሙ“…. የኤርትራ ጥያቄ በመገንጠል ደረጃ ሳይሆን ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብና ዕድል ጋር በተሳሰረና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በተቀራኘ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረግ” ያሻል በሚል፣ በአማራጭነት ፌደራላዊ ትስስርን አመላክቷል።

በመላ ሀገሪቱ፣ ኤርትራንም ጨምሮ፣ ማንኛውም የፖለቲካ አማራጭ አለኝ የሚል የፖለቲካ ስብስብ ሁሉ በነፃ የመደራጀት፣ አማራጭ የሚላቸውን የፖለቲካ አስተሳሰቦቹን በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የማቅረብና ሕዝብም የቀረበለትን አማራጭ በነፃ መርምሮ ከዘለቄታው ጥቅሙ አኳያ ይበጃል የሚለውን ያለምንም ተፅዕኖ የሚመርጥበትን ሁኔታ መፍጠር የግድ መኖር ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነው በሚል አምኖ ዴሞክራሲን መሠረት ያደረገን ሂደት እንዲኖር የመፍትሄ መንገድ ጠቁሟል። ይሁን እንጂ በሻዕቢያና ህወሓት እንደተደረገው፣ አማራጮቹ በግልጽ የሚቀርቡበት ሁኔታ ሳይመቻች ሕዝብ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመደራጀት ነፃነቱ በታቀበበት፣ በጠመንጃ የደረጀው ኃይል ሌሎችን የፖለቲካ ኃይሎች በነፍጥ እየደፈጠጠ ባለበት፣ የአንድን ለመገንጠል የተነሳን ድርጅት ነጠላ አስተሳሰብና ፍላጎትን እንደ ሕዝብ ፍላጎትና እምነት አስመስሎ በመጫን ዘላቂ ሰላምንና መረጋጋትን ማምጣት አይቻልም ብለናል፤ አልተቻለምም። “ነፃነት ወይስ ባርነት” በሚል አማራጩን በማጨለም በሚደረግ የይስሙላ ድምፀ-ውሳኔ፣ ዘላቂ ሰላም፣ ልማትንና ብልጽግናን ማምጣት አልተቻለም። ይህን የአንድነትና የዴሞክራሲ መንገዳችንን ያልወደዱልን ሻዕቢያና ህወሓት/ኢህአዴግ፣ የአስተሳሰብ ልዩነትን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሕዝብ እንዲመረምረውና እንዲወስንበት ለማቅረብ ባህሪያቸው የማይፈቅድላቸው ናቸውና ድርጅታችን ከተመሠረተበት ወቅት ጀምረው ለማደናቀፍ፣ ለማጫጫትና ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፤ ይህ ነው የማይባል ጉዳትም አድርሰዋል።

በኤርትራ ግንባሮች ውስጥ በየጊዜው በግፍ የተሰቃዩ፤ የተጨፈጨፉና መዳረሻቸው የጠፉ የዴሞክራሲ ኃይሎች ቁጥር እጅግ በርካታ ነው። አንድ ወጥ አስተሳሰብን እንጂ አማራጭን የማይቀበሉት እነዚህ ኃይሎች፣ በውስጣቸው የተነሱ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎችን ያመከኗቸው፣ የእንቅስቃሴዎቹ መሪዎች ናቸው ያሏቸውን አባላት ሁሉ በመጨፍጨፍና ድራሻቸውን በማጥፋት እንደሆነ ይታወቃል። ስለሆነም፣

ዴሞክራሲያዊው ትግል እግር ሰዶና ጠንክሮ ዘላቂ መፍትሄን ለመፍጠር ሳይችል ከጭቆና ወደ ጭቆና፣ ከግፍ አገዛዝ ወደ ግፋዊ አገዛዝ ሕዝባችን እንዲሸጋገር ሆኗል።

በ1983 ዓ. ም (እኤአ በ1991 ዓ.ም)፣ በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ የነበረውን ፍጹም አምባገነናዊውን የመንግሥቱ ኃይለማርያም መንግሥት፣ በጠንካራ ሕዝባዊ ትግል ከተዳከመ በኋላ፣ በባዕዳን ግዙፍ እገዛና ተሳትፎም በተካሄደ ወታደራዊ ጥቃት በመጣል በአስመራና በአዲስ አበባ ሥልጣን የተቆጣጠሩት ሻዕብያና ህወሓት፣ “ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ሥር ነበረች፣ ኤርትራ ከቅኝ ግዛት ነፃ ከመውጣት የተለየ ሌላ አማራጭ የላትም” በማለት ሀገሪቱን ከሁለት ሊከፍሉ ሲነሱ፣ ከነሱ አስተሳሰብ የተለየ መፍትሄ ይዘው ሊመጡ ይችላሉ ብለው ያሰቧቸውን የፖለቲካ ኃይሎች ነበር የመጀመሪያ ጥቃታቸው ዒላማ ያደረጓቸው። ኢሕአፓንና ኢህአሠን በመሣሪያ ኃይል ለማጥፋት ከሱዳን ጋር ተባብረው ዘመቱባቸው። ከዚያም ኢሕአፓ እንደ ፖለቲካ ድርጅት በሀገር ውስጥ እንዳይንቀሳቀስ አገዱት። በተመሳሳይ መንገድ ዕገዳ የተደረገባቸው ሌሎች ድርጅቶችም አልታጡም። ኢሕአፓንና ሌሎችን በተባባሪነት ሊሠለፉላቸው የማችሉ ናቸው ብለው የገመቷቸውን ድርጅቶችን በእንደዚህ ዓይነት እርምጃ ከፖለቲካ ሂደቱ እንዲነጠሉ በማድረግ በሀገሪቱ ብቸኛና ፍጹም ፈላጭ ቆራጮች በመሆን ኢትዮጵያን ከሁለት የመክፈል ህልማቸውን፣ ከታሪክ አኳያ ዘላቂ ሊሆን ባይችልም፣ ለጊዜው እውን አድርገዋል።

ኤርትራ ተቆርሳ ከጣሊያን ቅኝ-ገዥዎች ሥር በቆየችበት ወቅትና በኋላም እንግሊዝ በሞግዚትነት አካባቢውን በምታስተዳድርበት ጊዜም ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተነጥላ ለየት ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ቆይታ ነበር። ሕዝቡ ለሀገራዊ አንድነቱ ታግሏል፤ ተመልሶም በአንድነት ኢትዮጵያዊነቱን ተቀዳጅቶ ኖሯል። የዛሬው አዲስ ሊሆን አይገባም። አሁን ሁለቱ ፀረ-ኢትዮጵያ ሤረኞች፣ ኢሳይያስና መለሰ ዜናዊ፣ የዓለም-ዓቀፉ ፀረ-አንድነታችን ሤራ ተባባሪና መሣሪያዎችም ሆነው በኤርትራ ውስጥ የሚኖረውን የሕዝባችን ክፍል ለጊዜው ተነጥሎ እንዲቆይ አድርገዋል። በግብፃዊው ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ መሣሪያነት፣ በወቅቱ የአሜሪካው መንግሥት ባለሥልጣናት አቀነባባሪነት ግንጠላው ዕውቅና እንዲያገኝ ለማድረግ ተጥሯል። ኢትዮጵያውያን ግን በኢዴኃቅ አስተባባሪነት ተግባሩን ከዳር እስከዳር ተቃውመውታል። የተቃውሞ አቋማቸውንም ለተባበሩት መንግሥታት ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔ የወቅቱ ምክር ቤት ሰብሳቢ ለነበሩት በሠነድ አቅርበዋል። መቼም ቢሆን በኢትዮጵያ ሀገራዊ ጥቅምና አንድነት ላይ ሊወስን የሚችለው ሉዓላዊነቱ የማይገረሰሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው። የፋሽስቱ ጣሊያን ወረራን አፅድቆብን የነበረው የዚያን ጊዜው “ሊግ ኦፍ ኔሽንስ” ይባል የነበረው፣ በኋላ በተባበሩት መንግሥታት ማኅበር የተተካው መሆኑን ላንድአፍታም ልንዘነጋው አይገባንም። የኢትዮጵያ ባለቤቶች ደግሞ ዛሬም እኛው ዜጎችዋ ብቻ ነንና ይህንኑ መብታችንን መቼም ቢሆን ለማንም አሳልፈን እንደማንሰጥ ያልገባቸው ካሉ እንዲያውቁት ያስፈልጋል።

ዛሬ ሀገራችን ከሁለት ተከፍላ በሁለት አምባገነኖች መዳፍ ሥር ትገኛለች። በሰሜኑ የዘመናችን ፈርዖን የሚሰቃየው ወገናችን ‘የነጻነት’ን አየር መተንፈሱ ቀርቶ ዛሬ ኤርትራ የግፍ አገዛዝ የሰፈነባት፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በፍጹም የማይታወቅባት፣ ስደት የተበራከተባትና ግዞት የሰፈነባት፣ ጦርነት እንጂ ሰላም

የማይታይባት፣ ርሃብና እርዛት የጠነከሩባት ሥፍራ ሆናለች። በአሽባሪውና በአምባገነኑ በመለስ ዜናዊ ሥር የሚማቅቀው ከመረብ ወንዝ በስተደቡብ ያለው ክፍል ደግሞ ሰላም የጠፋበት፣ የህዝብ መብት የተነፈገበት፣ በብዙኃን ስም የአንድ ፓርቲ ሥርዓት የነገሠባት፣ የብሄሮች መብት ተከብሯል ተብሎ እየተለፈፈ ዜጎች በእኩልነት የማይታዩባት፣ በሚናገሩት ቋንቋ ላይ የተመሠረተ አድሎና ልዩነት የሚደረግባት፣ ከአፋር እስከ ኦጋዴን፣ ከትግራይ እስከ ሞያሌ ጠረፍ ሀገራችን በጦርነት የምትናጥበት፤ ነባር እስር ቤቶች በፖለቲካ እስረኞች ተሞልተው የተጨናነቁበት፣ የድብቅ እስር ቤት በየቦታው የተበራከቱበት፣ ከስድስት ሚሊዮን በላይ ሕዝባችን አሁንም የውጭ ርጥባን-ለጋሾችን እጅ የሚጠብቅባት፣ አራሹ ገበሬ አሁንም የመሬቱ ባለቤት ያልሆነባት፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የሀገሪቱ ሕፃናት የዕለት ጉርሳቸውንና መጠለያ የማያገኙባት፣ ያጣና የነጣው ደሃ ሕዝብ የበረከተባት፣ ገዥው ክፍል በዝርፊያ ከብሮ የሚናጥጥባት ሀገር ሆናለች። የሀገሪቱ ገበሬ በእርሻ መሬት እጦት ቀዬውን እየተወ በሚሰደድባት ሀገር በሚልዮን ጋሻዎች የሚቆጠር ለም መሬት ለውጭ ኩባንያዎችና ከበርቴዎች የሚቸበቸብባት፣ ውሃ-ገብ የሆኑ በሀገራችን ምዕራባዊ ወሰን የሚገኙ ለም መሬቶች ለሱዳን በወሮታ መልክ የሚሰጥባት፣ በአጠቃላይ ሀገራችን ለበርካታው ሕዝባችን የምድር ሲኦል የሆነችበት ጊዜ ነው።

እነዚህ መንታ አምባገነኖች በጫሩት የእርስ በርስ ጦርነት፣ መቶ ሺህ የሚጠጉ ወገኖቻችን ሲያልቁ፣ ሌሎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የአካል ጉዳተኞች ሲሆኑ፣ የልማት አውታሮች ሲፈራርሱ፣ በቢልዮን ብር የሚቆጠር ንብረት እንዲጠፋ ሆኗል። የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህል ትሥስሩ ጠንካራ በሆነው ሕዝብ ውስጥ ጥርጣሬና ጥላቻን አራግበዋል። ሁለቱም አምባገነኖች በሕዝብ ላይ ግፍና በደል ፈጽመዋል። ይህንን በዝርፊያ ከተገኘ ሃብትና ንብረት ክፍያ ጋር የተያያዘ ጠብና ግጭት ምክንያት በማድረግ አንደኛው የሌላኛውን ተቀናቃኝ በመሣሪያነት ለመጠቀም ሲሞክርና ሲኳትን ይታያል። የሻዕቢያው መሪ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን አንድነት የሚሻ በማስመሰል ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የሚሆኑ ቃለ ምልልሶችን ያድርግ እንጂ "የቀበሮ ባህታዊ" መሆኑን፣ ከፍተኛ ጥላቻውን ሲያሳያቸውና ሊያጠፉቸው ሲምልና ሲገዘት መኖሩን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊነት የሚስቱትና የሚዘነጉት አይሆንም። ፈርዖኑ ለኢትዮጵያውያን አዲስ ፍቅር ይዞት እንዳልሆነ ያለፉ ተግባሮቹ ምስክሮች ናቸው። ሌላው ቀርቶ በአንድ ምላሱ የኢትዮጵያን አንድነት እንደሚደግፍ እያስመሰለ ሲማለል በሌላ በኩል ደግሞ በራሱ በሻዕቢያ በሚደገፉና "በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ሥር ነን፣ መገንጠል አለብን" የሚሉና ኢትዮጵያን እንደገና ለመከፋፈል ለሚጥሩ ድርጅቶች በሰጠው ቃለ ምልልስም፣ የህወሓት/ኢ.ህአዴግን የይስሙላ ህገ-መንግሥት፣ አንቀጽ 39ን ተጠቅመው "ነፃ" እንዲወጡ እያበረታታ ነው። የሚያምንበትና መመሪያ አድርጎ የያዘውም ስለሆነ!!

ህወሓት/ኢ.ህአዴግ ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግስ፣ ያለ የሌለውን ሃይል፣ በተለይም "በሜካናይዝድ ክፍሉ" አጅቦ አገሪቱን እንዲቆጣጠር የረዳው፣ በለንደን ኮንፈረንስ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ ድርጅቶችን እንዳይካተቱ ከህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ጋር ሆኖ አሻፈረኝ በማለት ከፖለቲካው መድረክ እንዲገለሉ ያደረገው፤ በዘር የመደራጀትን መርሃ-ግብር በሎሌነት ባሰለፈው በህወሓት አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ መመሪያ በማድረጉ ተኩራርቶ "ለኢትዮጵያውያን የመቶ ዓመት የቤት ሥራ

ሰጠኋቸው” ብሎ የተመጻደቀው፤ የባድመ ጦርነት እስኪጀመር ድረስ ሀገሪቱን በህወሓት/ኢህአዴግ የግፍ ቀንበር ሙሉ በሙሉ እንድትገባ በመላ ሀገሪቱ ነፍሰ ገዳዮቹን እያሰማራ ሕዝባችንን ያሸበረው፣ የሀገራችንን ንብረት በማናለብኝነት የመዘበረው ሻዕቢያና መሪው ኢሳያስ ነበር እኮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ የጦር ኃይል ባልደረባ የነበሩና ሲቪል ኢትዮጵያውያንን በጨለማ ጉድጓድ ውስጥ ከ19 ዓመት በላይ አስሮ እያሰቃየ ነው የቆየው። ሻዕቢያ የባድመ ጦርነት ከተቀሰቀሰ በኋላ እንኳን የአሸባሪውን የህወሓት መንግሥት እመቃ ሸሽተውና በኢሳያስ መንግሥት ተረድተን ፀረ-ህወሓት ትግል እናደርጋለን ብለው ወደ ኤርትራ የተሰደዱት ሀገር ወዳድ ኢትዮጵየውያን መካከል ስንቶቹን መዳረሻቸው እንደጠፋ ለመቁጠር እንኳን አስቸጋሪ ሆኗል። በህይወት ያሉትም ፍሬ ያለው እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ ተሰናክለውና በየማዕከሉ ታጉረው ዓመታት እያስቆጠሩ ነው። የተወሰኑ የቀድሞ የኢሕአፓ አባላትም፣ የድርጅቱን ምክር አልሰማ ብለው፣ በተመሳሳይ ዕምነትና ተስፋ በሱዳን በኩል ወደ ኤርትራ እንዳመሩ፣ ከዚያም በኋላ ያሳዩት የሀገር ወዳድነት መንፈስና ነፃ ሆነው ለማሰብ መሞከራቸው ለኢሳያስና ጋሻ ጃግሬዎቹ ስላልጣማቸው በርካታው ለእስር፣ ለስቃይና ግድያም ተዳርገው እንዳለቁ የሚታወቅ ነው።

ገና ከጅምሩ ኢትዮጵያዊነቱን አንግቦ አፍቃሪ-አንድነት መሆኑንም ሳይደብቅ እያሳወቀ የተነሳን ታጋይ ኃይል ሁሉ ቢችል በተዕዕኖ የሻዕቢያን እምነት አራማጅና አቀንቃኝ እንዲሆን ካልሆነም እንዲዳከምና እንዲጠፋ በተለያየ መንገድ ሲሠራና ሲያሤር የኖረው ሻዕብያና አምባገነኑ መሪው ኢሳያስ አፈወርቂ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ)ን ጥንስስ ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ሳህልን (ከቀይ ባህር ጥግ የነበረውን ክፍል) ለቆ ጉዞውን ወደ አሲምባ እንዳያደርግና ትግሉን እንዳይጀምር አግቶ ሲያቆይ፣ በአንጻሩ በዚሁ ጊዜ ውስጥ ነው የኤርትራን ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ብሎ የተቀበለውንና ለዚህ የመገንጠል ዓላማው ተባባሪ ሊሆነኝ ይችላል ያለውን ህወሓትን አስልጥኖ በማስታጠቅ በትግራይ ለእንቅስቃሴ ያበቃው። በተከታታይ ዓመታትም፣ ለህወሓት ወታደራዊ ስልጠና ሲሰጥና ሲያስታጥቅ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በድርጅታችን ላይ ከፍተኛ የማዳከም ሤራዎችን ሲፈጽም ቆይቷል፤ በተለያዩ የውጭ ሀገራት በፀረ-ኢሕአፓ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ተንቀሳቅሷል፣ የደርግን ሠራዊት እየከዱ ወደ ሕዝባዊው ትግልና ወደ ሠራዊታችን እንዲላኩ ይጠይቁ የነበሩ ወታደሮችን መሣርያቸውን እየነጠቀ መዳረሻቸውን አጥፍቷል፣ ለሠራዊታችን ከውጭ በአባላት ጥረት የሚገኙና በኤርትራው ግንባር በኩል የተላኩ መሣሪያዎችን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም አስቀርቷል። ደግሞም ከህወሓት ጋር ወታደራዊ ትብብር በማድረግ ሠራዊታችንን በፊት በትግራይ ውስጥ ወግቷል፣ በኋላም በበጌምድርና በጎጃም ኢህአፓን ለማጥፋት በተደረጉ ጦርነቶች በመተማ በኩል ከህወሓት ኃይሎች ጋር ተንቀሳቅሶ የሻዕቢያው ጦር በኢሕአፓና ኢሕአሠ ላይ የሚይረሱ ጉዳቶችን አድርሷል።

ዛሬ፣ ለሀገራችንና ለሕዝባችን አንድነትና ያልተሸራረፈ ስብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር የምናደርገው ትግል ውስብስብ ያለ ቢሆንም፣ ራዕያችን ካልጠራና ወዳጅ ጠላታችንን በደንብ ለይተን ካላወቅን “ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሁልጊዜ ሲያለቅስ ይኖራል” እንዲሉ ከአዙሪቱ መውጣት ያቅተናል። “ከሰማይ ዳቦ

እንዲወርድ” እየጠበቅን አገራችን የገባችበትን አስከፊ ውድቀት፣ ጦርነትና ሕዝባችን የታሰረበትን የግፍ ሰንሰለት መበጣጠስ አንችልም። መለሰ ዜናዊና ኢሳያስ አፈወርቂ ለኢትዮጵያ ጥፋትን እንጂ ልማትን እንደማያመጡ እስከዛሬ ድረስ አለመገንዘብ ጤነኛ አዕምሮ ካለውና የኢትዮጵያን አንድነት ከሚሻ ሀገር-ወዳድ የሚጠበቅ አይሆንም።

የሁሉም ነገር ቁልፉ ያለው በሕዝባችን እጅ መሆኑን ለአንዳፍታም ልንዘነጋው አይገባም። ለታሪካዊቷ ሀገራችን አንድነት፣ ለዴሞክራሲና ለፍትኅ እየታገልን ስለአንድነቷ መስማት ከሚያባንነው፣ ዋናው ዓላማውም አንድነቷን ማፍረስ ከሆነው፣ ፍትህን ከሚነሳና በማንኛውም መሥፈርት የአምባገነንነትን ወሰን ከዘለለው በመጠጋትም ሆነ በማበር ችግሮቻችንን ይበልጥ ማባባስ እንጂ መፍትሄ ማግኘት ፍፁም አይቻለንም። ለአንድነት እየቆምን አንድነታችን ጭራሽ ከማይዋጥለት ከፋፋይና አፍራሽ ጋር ልንዛመድ አንችልም፣ እንደ አጋሙ እሾህ አልባ ስለማይሆንልን ሁሌም እንዳልታደለው ቁልቋል እየወጋ ያስለቅሰናል እንጂ የሚፈይደው አንዳችም ቁምነገር የለውም።

በተቃዋሚነት ተሠልፈው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉት የኢትዮጵያን ሀገራዊ አንድነት የሚሹ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ ትኩረታቸውን የመለሰ ዜናዊ መንግሥት በማስወገድ ላይ አድርገው፣ ከጥቃቅን ልዩነቶች መጠቅ ብለው፣ እራሳቸው ተባብረውና ሕዝብን አስተባብረው፣ በሕዝብ ትከሻ ላይ የሚጋልበውን አምባገነን ቡድን አሽቀንጥረው ለመጣል በቁርጠኝነት መነሳት የመጀመሪያ ተግባራቸው መሆን ይገባዋል። ከዴሞክራሲያዊ የአንድነት ኃይሎች ጋር ለመተባበርና አብሮ ለመሥራት ሳይጥሩ በሕዝብ ላይ፣ በወገን ላይ፣ አምባገነንነቱን አንሰራፍቶ ከተቀመጠ ቡድንና ግለሰብ ጋር በመወዳጀት ትብብሩን መሻት ቢያንስ መጭውን ጣጣ ግምት ውስጥ አለማስገባት ነው። የቅርብ ተመክሮአችንን እንኳን ብንመረምር ኢሳያስ እንዲፈጠሩለት የሚፈልጋቸው “ኅብረቶች” የኢትዮጵያ ስም እንዳይኖራቸው ሀገራዊ ቋንቋችንን እንዳይጠቀሙ ለማድረግ ነው የሚጥረው። የዴሞክራሲን መሠረት ለመጣልና ያለፈን ቁርሾ አስወግዶ የዘላቂ ሰላምንና የአንድነትን ጎዳና ለመያዝ፣ በኤርትራም ይሁን በቀረው የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኙ የዴሞክራሲ ኃይሎች ሁሉ ትግላቸውን አስተባብረውና አቀናጅተው የጭቆናን፣ የሁከትን፣ የግፍን፣ የጠብን፣ የጥላቻን፣ የመለያየትን መንስዔዎች ከመሠረታቸው መንግለው ለማስወገድ መነሳት አለባቸው። አንዳቸው ከአንዳቸው አምባገነን ጋር ቢያብሩ፣ አብረው ቢሠሩ፣ የመከራንና የስቃይን ጊዜ የሚያራዝሙ እንጂ የሕዝብን ለቅሶና እንባ የሚያደርቁ አይሆንም።

በተባበረ ሕዝባዊ ኃይል፣ የዜጎቿ እኩልነትና አንድነቷ
የተረጋገጠ ኢትዮጵያ ትመሰረታለች!!

## ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!